# *“አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ሕዝባዊ ንቅናቄ ዓርማና መግለጫ፡*

*የኢትዮጵያ ካርታ፡* በአርማው ላይ የሚታየው የኢትዮጵያ ካርታ ከዛሬ 25 ዓመት በፊት ያለአግባብ የተገነጠለችዋን ኤርትራ ለየት ባለ ቀለም አስቀምጠናል። ንቅናቄው የኤርትራን ሀገርነት ወደፊት ኢትዮጵያ በሕዝበ ውሳኔ እውቅና ብትሰጥም ከኤርትራ ጋር ቀና ግንኙነት ለመፍጠር ያለምንም ቅድመ ሁናቴ ኤርትራ አሰብ ወደብን ለኢትዮጵያ መመለስ አለባት ብለን እናምናለን። በመሆኑም በኤርትራ ግዛትና በአሰብ መካከል የወሰን መስመር አድርገናል። ይህ የአሰብ ክልል ለኢትዮጵያ ይገባታልና የኤርትራ ግዛትነቱን ባለመቀበላችን ለብቻው ከኢትዮጵያ ግዛት ጋር በሚኖረው አቀማመጥ አካተነዋል።

*ኢትዮጵያን የከበቡት የተያያዙ እጆች፡* ኢትዮጵያ በጀግኖቿ ደምና አጥንት የተከበበች መሆኗን ሲያሳይ በሌላ በኩል ሁሉም ዜጎቿ በአንድነት እጅ ለእጅ ተያይዘን በ “አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ሕዝባዊ ንቅናቄ” ዳግም ትንሳዬዋን እንደምናበስር ያለንን ተስፋ ያንጸባርቃል።

*ኢትዮጵያን የከበባት ዘንባባ፡* ዘንባባው ልምላሜን፡ ዕድገትንና ሰላምን ያሳያል። አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ሕዝባዊ ንቅናቄ ይዞት የተነሳው ዓላማ ህያው መሆኑንና የልጆቿ የሆነች ኢትዮጵያ ወደ ልምላሜና ሰላም ጎዳና እንደምታመራ ያለውን የወደፊት ራዕይና ተስፋ ያሳያል።

**ኢትዮጵያን ዙሪያ የከበባት ሰንደቅ ዓላማ፡** የኢትዮጵያን ካርታ ዙሪያዋን የከበበው አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ዓርማችን የአንድ ኢትዮጵያ ሀገራችን ብሔራዊ መለያችንና የነጻነት ዓርማችን ዘለዓለማዊ መሆኑን ያንጸባርቃል።

*አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ሕዝባዊ ንቅናቄ ፡* በቅስት መልክ ከላይ እና ከታች የተጻፈው የንቅናቄው ስያሜ መሆኑን ይገልጻል።

ኢትዮጵያችን፡ ኢትዮጵያ ካርታ መሀሉ ላይ በቢጫ የተጻፈው ኢትዮጵያችን የሁሉም ብሔር/ብሔረሰቦች ማዕከል/አስኳል መሆኗን ለማስረገጥና የልጆቿ እና የሕዝቧ የሆነች ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ እንደምንገነባ ያለንን ተስፋ ያመላክታል።